# ወይ ንቀት፣ ወይ ጊዜ!

መንግስቱ ደፋር
(ፍራንክፈርት - ጃንዋሪ - 2012)

ንገረኝ አልክ አሉ፣ ስረ-መሠረትክን፣
ጥንተ ሥሪትህን፣ አንጋች መሆንህን፣
ሹምባሽ፣ ባንዳነትክን፣ ለጁንታው ማደርክን፣
መንታ ዜግነትክን፣ አረንዛ ሥሪትክን።

ንገረኝ ካልክማ፣ ልንገርህ በወጉ፣
ጥቁር ነው ምላስህ፣ ፈነቢስ ነው ወጉ፣
መሠሪ ነው ልብህ፣ የክህደት መፃጉ፣
አሳሳች ነው መለክህ፣ መንትያ ማረጉ።

አንተው ካመጣኸው፣ ልንገርህ ሥራህን፣
ሾተላይ ነትክን፣ ዘር የማጣፋትክን፣
ሸሽግ  ባንዳነትክን፣ የጎጥ ማቀነትክን፣
በቀትር ነጣቂ፣ ሌት ቀሳፊነትክን።

አንተው ካመጣኸው፣ ንገረኝ ካልክማ፣
በሩቁም በቅርቡም፣ ዝናህ ከናኘማ፣
ክህደትህ ከለማ፣ ሥራህ ከተግማማ፣
ናላህ  ውሉን ስቶ፣ ትንፋሽህ ገለማ፣

ወትሮስ መች ፈጥሮብህ፣ ሃቅ ለመናገር፣
ብርዝ ነው መንፈስህ፣ ጅረት የሚሻገር፣
ጥልቅ ነው ተልእኮህ፣ ትውልድ የሚያማትር፣
የወያኔ ሥሪት፣ የደርግ መጢቃ፣ የሻቢያ ደምስር።

ወትሮስ ሀበሻነት፣ ምን ስሜት ሊኖርህ፣
ያደግከው ውረኒ፣ ሥርዓት አልባ ሆነህ፣
የጎጥ ጥንስስ ገፈት፣ የሰው ደም ጨልጠህ፣
ብትገለማ አይደንቅም፣ የደርግ ጡት ጠብተህ።

እንዲህ ነው ልጅ ማለት፣ እንዲህ ነው ማደጎ፣
ሲመሰክር ማየት፣ ባደባባይ ሸንጎ፣
የታሪክ ግማዱን፣ አቻውን ፈልጎ፣
ጥብቅና ይቆማል፣ ላንቃውን ሰንጎ።

በደም የጨቀየ፣ ብእር የተፋውን፣
ወገን የመተረ፣ ህይወት ቀሳፊውን፣
ሀገር ያጠፋውን፣ ትውልድ የፈጀውን፣
ታሪክ ነው ይለናል፣ ናዚ ያቀለመውን።
የቁም ቅዠት ክታብ፣ የጁንታ ኑዛዜ፣
የሌጊዮን ቅጥፈት፣ የክህደት አባዜ፣
የቀሳፊ ምላስ፣ የሀገር ትካዜ፣
ታሪክ ነው ተባልን! ወይ ንቀት! ወይ ጊዜ!

**እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ!!**



EthioLion.com